1. “እውነት እላችኋለሁ የሰው ልጅ በመንግስቱ ሲመጣ እስኪያዩት ድረስ እዚህ ካሉት ውስጥ ሞትን የማይቀምሱ አሉ።” ተብሎ የተነገረለት ሐዋርያ ማን ነው?
ሀ) ዮሐንስ ፍቁረ እግዚእ ለ) ጴጥሮስ ሐ) እስጢፋኖስ መ) ያዕቆብ

2. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በርጠሜዎስን ያዳነው በየት ነው?
ሀ) ገሊላ ለ) ቅፍርናሆም ሐ) ኢያሪኮ መ) ናዝሬት

3. ጌታችን "የሰው ልጅ" ብሎ በእርሱ ላይ ስለሚደርሱት መከራዎች ከጠቀሳቸው ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው?
ሀ) ለካህናት አለቃዎችና ለጻፊዎች ዐልፎ ይሰጣል
ለ) የሞት ፍርድ ይፈርዱበታል
ሐ) ቀይ ግምጃ ያለብሱታል
መ) ይተፉበታል
ሠ) መልስ የለም

4. "በዚኽ መኖር ለኛ በጎ ነው" ያለው ሐዋርያ የቱ ነው?
ሀ) ጴጥሮስ ለ) ዮሐንስ ሐ) ያዕቆብ መ) ኤልያስ

5. ጌታችን ወደ ደብረታቦር ተራራ ከወጣበት ምክንያት ውስጥ የማይመደበው?
ሀ) በቄሳርያ ከነቢያት አንዱ ብለውት ስለነበር ነቢያትን ጠርቶ የነቢያት ጌታ እንደሆነ ለማስመስከር ነው
ለ) በደብረታቦር የዘመነ መሳፍንቱ ባርቅ ሲሳራን ድል ስላደረገው ምሳሌውን ለመፈጸም ነው
ሐ) ነቢዩ ዳዊት በመዝሙሩ ታቦርና አርሞንኤም በስምህ ደስ ይላቸዋል ብሎ ስለተናገረ ትንቢቱን ለመፈጸም ነው
መ) መልሱ አልተሰጠም

6. ጌታችን ወደ ደብረ ታቦር ሲወጣ ይዟቸው ከወጣቸው ሐዋርያት ውስጥ ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ) ጴጥሮስ ለ) ይሁዳ ሐ) ያዕቆብ መ) ዮሐንስ

7. ጌታችንና ሐዋርያቱ ከታቦር ተራራ በወረዱበት ጊዜ እስከ ትንሳኤው ድረስ ያዩትን ለማንም እንዳይናገሩ ያዘዛቸው ለምን ነበር?
ሀ) ውዳሴ ከንቱን ስለማይሻ
ለ) መከራን ወደኋላ አድርጎ ክብርን መናገር ስለማይገባ ነው
ሐ) ምትሐት ያሳያል ብለው ሰዎች በእርሱ እንዳይሰናከሉ ነው
መ) ሁሉም

8. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደብረታቦር ግርማ መለኮቱን ሲገልጥ ሁለቱን ነቢያት የጠራበት ምክንያት የቱ ነው?
ሀ) ሰዎች ሙሴ ወይ ኤልያስ ነው ይሉ ስለነበር የነርሱ አምላክ እንጂ እነርሱን እንዳልሆነ ለማሳየት
ለ) የሙታን እና የሕያዋን አምላክ መሆኑን ለማሳየት ከሙታን ሙሴን ሞትን ካልቀመሱት ደግሞ ኤልያስን መርጧል
ሐ) መንግስተ ሰማያት ላገቡትም ላላገቡትም እንደሆነች ሲያጠይቅ ካገቡት ሙሴን ካላገቡት ደግሞ ኤልያስን መረጠ
መ) ሁሉም

9. "ዐይናቸውንም አቅንተው አዩ፤ ነገር ግን ከጌታችን ከኢየሱስ በቀር ያዩት ማንም አልነበረም። " ይኽ የሆነበት ምክንያት?
ሀ) ሙሴ እና ኤልያስ በዛው ቢሆኑ ኖሮ "የምወደው፣ በእርሱም ደስ የሚለኝ ልጄ ይህ ነው " የሚለው ቃል ለማን እንደተነገረ ግራ ይጋቡ ነበር
ለ) ሙሴና ኤልያስ የታዩት በምትሀት ስለነበር
ሐ) ሐዋርያት ስለፈሩ ከዚህ በኋላ ሙሴን እና ኤልያስን ማየት አልቻሉም
መ) ሁሉም

10.ደቀ መዛሙርቱ ጋኔኑን ማውጣት ያቃታቸው ለምንድን ነው?
ሀ)ስለእምነታቸው መጉደል
ለ) ይህ አይነቱ ያለጾም እና ያለጸሎት ስለማይወጣ
ሐ) ጨረቃ ስላልወጣ
መ) ሀ እና ለ

11. "ነገር ግን እላችኋለሁ፣ ኤልያስ ፈጽሞ መጥቷል " ብሎ ጌታ የተናገረለት ማን ነው?
ሀ) ነቢዩ ኤልያስ
ለ) መጥምቁ ዮሐንስ
ሐ) ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ
መ) ራሱ ጌታችን፣ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ

12.ሙሴ ሰው ሚስቱን ሲፈታ የምትፈታበትን ነውር የሚናገር ደብዳቤ ሰጥቶ እንዲፈታት ካዘዘበት ምክንያት ውስጥ የማይመደበው የቱ ነው?
ሀ. ስለ ልባቸው ክፋት ሲል ነው
ለ. እርስ በእርስ እንዳይገዳደሉ ሲል ነው
ሐ. የእስራኤላውያን የሕዝብ ቁጥር እንዲበዛ አንድ ወንድ ከብዙ ሴቶች መውለድ ስለነበረበት ነው
መ. መልሱ አልተሰጠም

13.ጌታችን ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን የሚያሰናክል አህያ የሚፈጭበት ወፍጮ በአንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቁ ባሕር ቢሰጥም ይሻለዋል ስላለበት ምክንያት ልክ ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ) አንድ ክርስቲያን በጉዞው ሁሉ ለሌሎች በጎ ምሳሌ እንጂ ማሰናከያ መሆን እንደሌለበት ሲናገር ነው
ለ) የሃይማኖት መሪዎች ለምእመናን በሆ ምሳሌ መሆን አለባቸው ሲል ነው
ሐ) ወልድ ዋህድ ብለው ካመኑ ምእመናን አንዱን ያሰናከለ ሰው ራሱን ማጥፋት እንደሚገባው ሲናገር ነው
መ) ከምእመናን መካከል አንዱን ያሳተውን ሰው ጽኑ ቀኖና ሰጥተው ባሕር በተባለው የንስሐ እንባ ቢያሰጥሙት ይሻለዋል

14.ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሁሉ በላይ መሆን ለሚሻ ምን ትምህርት አስተላለፈ
ሀ) ሁሉን ይዘዝ ይምራ ለ) የሁሉ አገልጋይ ይሁን ሐ) የሁሉ ሎሌ ይሁን መ)ለ እና ሐ

15. የማርቆስ ወንጌል 10፥14፤ “ነገር ግን ኢየሱስ፦— ሕፃናትን ተዉአቸው፥ ወደ እኔም ይመጡ ዘንድ አትከልክሉአቸው፤ መንግሥተ ሰማያት እንደነዚህ ላሉ ናትና” ሲል ምን ለማለት ነው?
ሀ) ቂም በቀል የማያውቁ
ለ) ጨዋታን የሚያበዙ
ሐ) ፍፁም ፍቅርን የተላበሱ
መ)ሀ እና ሐ

16. በማርቆስ ምዕራፍ 10 ላይ ያለው ባለፀጋ ለምን አዝኖ ተመለሰ?
ሀ) ምንም ንብረት ስለሌለው
ለ) ብዙ ንብረት ስለነበረው
ሐ)ብዙ ግመሎች ስለነበሩት
መ) ሁሉም

17. ጌታችን ለዘብዴዎስ ልጆች እናት ሲመልስላት እኔ የምጠጣውን ጽዋ... በማለት ሞቱን በጽዋ መስሎ የተናገረበት ምክንያት የቱ ነው?
ሀ. ጽዋ የሚጠጣው በተራ እንደሆነ ሞትም በተራ ነውና ነው
ለ. ጽዋ እንዲያፋቅር የክርስቶስ ሞት ያፋቅራልና ነው
ሐ. ጽዋ ፈጥኖ እንደሚጨለጥ ጌታችንም የሞቱን ጽዋ ይጨልጥ ዘንድ ፈጥኖ ተነስቷልና ነው
መ. ሁሉም

18. የጤሜዎስ ልጅ ጌታችንን አይኑን እንዲፈውሰው የጠራው ማን ብሎ ነው?
ሀ) የዳዊት ልጅ ለ) የናዝሬቱ ኢየሱስ ሐ) መምህር መ) አምላኬ ሠ) ሀ እና ለ

19. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ በስሙ አጋንንት ስለሚያወጣው ሰው ምን አላቸው?
ሀ) በስሜ ተአምር ሠርቶ በቶሎ በእኔ ላይ ክፉ መናገር የሚችል ማንም የለምና አትከልክሉት
ለ) ስለማይከተለኝ ከእናንተ ጋር እንዳይሆን ከልክሉት
ሐ) ባልንጀራችሁ ሳይሆን ባላጋራችሁ ነው
መ) ወደእኔ አምጡት

20. ግመል በመርፌ ቀዳዳ ያሳለፈው ሐዋርያ ማን ነው?
ሀ) ቶማስ ለ) ታዴዎስ ሐ) ጴጥሮስ መ) ያዕቆብ

21. "ሁሉም በእሳት ይጣፍጣልና መሥዋዕት ሁሉ በጨው ይጣፍጣል " ሲባል እሳት እና ጨው የምን ምሳሌ ናቸው?
ሀ) እሳት የሃይማኖት፣ ጨው የፍቅር
ለ) እሳት የማብሰያ፣ ጨው የማጣፈጫ
ሐ) እሳት የሰማዕትነት፣ ጨው የድንግልና ሕይወት
መ) እሳት የሕብረት ሥራ፣ ጨው የግል ሥራ

22. "ዐይንህም ብታስትህ አውጣት " ሲባል ዐይን ማለት?
ሀ) የቅርብ ወዳጅ ለ) ሚስት ሐ) ዘመድ መ) ሁሉም

23. "መምህር ሆይ አንድ ሰው በስምህ አጋንንትን ሲያወጣ አየነው ስለማይከተለንም ከለከልነው አለው" ይህንን የተናገረው ማን ነው?
ሀ)ሐዋርያው ማቴዎስ
ለ)ሐዋርያው ዮሐንስ
ሐ)ሐዋርያው ቶማስ
መ)ሁሉም

24. በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 9 ላይ ጋኔን ይጥለው የነበረውን ሰው አባት ጌታ "ቢቻልህ ብለሃል፤ ብታምንስ ለሚያምን ሁሉ ይቻላል " ባለው ጊዜ የእርሱ ምላሽ ምን ነበር?
ሀ) "አቤቱ አምናለሁ"
ለ) "ከዚህ በላይ ማመን አይቻለኝም"
ሐ) "አለማመኔን እርዳው "
መ) ሀ እና ሐ

25. በማርቆስ ወንጌል በስድስተኛውም ቀን ወደ ተራራ ወጡ ሲል ከምን ጀምሮ ቆጥሮ ነው?
ሀ) ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት
ለ)ማን ይበልጣል ብለው ከተከራከሩበት
ሐ) ሰው እኔን ማን ይለኛል ብሎ ከጠየቀበት
መ)ሁሉም